

Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

# የተማሪ እና የቤተሰብ **የስደተኝነት ድጋፎች**

**ትምህርት ቤቶቻችን፦ ማንኛውም ልጅ—የስደተኝነት/የኢሚግሬሽን ሁኔታው(ዋ) ምንም ይሁን ምንም—መልካም አቀባበል የሚደረግበት፣ የሚከበርበት፣ እውቅና የሚሰጥበት፣እና የሚወደድበት ደህንነታቸው የተጠበቁ ቦታዎች ናቸው፤ ሆነውም ይቀጥላሉ።**

ዶ/ር ቶማስ ቴይለር፣ ሱፐርኢንተንደንት፣ ዲሴምበር 2024

## ቁልፍ የሆኑ እውነታዎች፦

- በስቴት እና በፌደራል ህግ መሠረት፣ ሁሉም ልጆች፣ ዜግነታቸው ወይም የመኖሪያ ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን፣ የኮሌጅ ካውንስሊንግ አገልግሎትን ጨምሮ ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል (K-12) ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው።
- ትምህርት ቤቶች የፍርድ ቤት ትእዛዝ ከሌለ በስተቀርያለ ወላጅ ፈቃድ  ከተማሪ ፋይል መረጃ አንስተው ለፌደራል የኢሚግሬሽን ወኪሎች እንዳይሰጡ የተከለከሉ ናቸው።
- ስደተኛ ቤተሰቦች ማወቅ እንዳለባቸው የማረጋገጥ መብት አላቸው።

### ICE ወይም ማንኛውም ከአካባቢ ህግ አስከባሪ ውጭ የሆነ ሌላ የህግ አስከባሪ ወደ ትምህርት ቤት ቢመጣ ምን ይደረጋል?

ICE ወኪል ወይም ሌላ ማንኛውም ከአካባቢ ህግ አስከባሪ ውጭ የሆነ የሕግ አስከባሪ አካል ተማሪን/ተማሪዎችን በሚመለከት ጉዳይ ወደ ትምህርት ቤት ከመጣ የሕንፃው አስተዳዳሪዎች መከተል ያለባቸው ጥብቅ ፕሮቶኮል አላቸው። እንደዚህ አይነት ጥያቄ ወይም ሁኔታ ሲከሰት ለቤተሰብ ይነገራል።

### ትምህርት ቤቶች ለ ICE ወይም ሌላ ማንኛውም ከአካባቢ ውጭ ለሆነ የህግ አስከባሪ አካል ስለ ቤተሰብ መረጃ ይሰጣሉ?

በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) እና የስቴት ህግ መሰረት ትምህርት ቤቶች  የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልደረሳቸው በስተቀር ያለ ወላጅ ፈቃድ ከተማሪ ፋይል መረጃ ለፌደራል የኢሚግሬሽን ኤጀንሲዎች እንዳይሰጡ የተከለከሉ ናቸው።

### ቤተሰቦች እንዴት መዘጋጀት ይችላሉ?

የኢሚግሬሽን ሁኔታ ስጋት ያለባቸው ቤተሰቦች የድንገተኛ ጊዜ እቅድ ሊዘጋጅላቸው እና በድንገተኛ ጊዜ ልጆቻቸውን መንከባከብ የሚችል ታማኝ የቤተሰብ አባል መሰየም አለባቸው። የድንገተኛ አስቸኳይ ጊዜ እቅድ እንዴት ማዘጋጀት እንደሚችሉ ለማወቅ እባክዎ ይህንን መመሪያ ያንብቡ፦ ተጠባባቂ ሞግዚት "Standby Guardianship"

ስለ ተጠባባቂ ህጋዊ ከለላ መረጃ

---

(ቆርጠው ያስቀምጡ)

## የእርስዎን መብቶች ይወቁ

ይህ ከስደተኞች የህግ ድጋፍ አገልግሎት ማዕከል የተሰጠ የመብቶች ናሙና ካርድ ነው። የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥምዎት የኢሚግሬሽን ጠበቃ ያማክሩ።

ሕገ መንግሥታዊ መብቶች አሉዎት፦

- የኢሚግሬሽን ወኪል በር ሲያንኳኳ በሩን አይክፈቱ።
- የኢሚግሬሽን ወኪሎች እርስዎን ለማነጋገር ከሞከሩ ለማንኛውም ጥያቄ መልስ መስጠት የለብዎትም። ዝም የማለት መብት አለዎት።
- በመጀመሪያ የህግ ባለሙያ/ጠበቃ ሳያማክሩ ምንም ነገር ላይ አይፈርሙ። የህግ ባለሙያ/ጠበቃ የማናገር መብት አለዎት።
- ከቤትዎ ውጭ ከሆኑ፣ የኢሚግሬሽን ኤጀንቱን ለመሄድ ነፃ መሆንዎን ይጠይቁ እና አዎ ከተባሉ፣ በእርጋታ ቦታውን ለቀው ይሂዱ።
- ይህንን ካርድ ለኢሚግሬሽን ኤጀንቱ ይስጡ። በቤትዎ ውስጥ ከሆኑ፣ ካርዱን በመስኮት በኩል ያሳዩ ወይም በበሩ ስር ያንሸራቱ።

በዩናይትድ ስቴትስ "5ኛው የሕገ መንግሥት ማሻሻያ" ባለኝ መብት መሠረት ካንተ(ቺ) ጋር ለመነጋገር፣ ለጥያቄዎችህ(ሽ) መልስ ለመስጠት፣ ወይም ማንኛውንም ሰነድ ለመስጠት አልፈልግም።

ለመግባት ከፍርድ ቤት ዳኛ ወይም ከማጅስትሬት የተፈረመበት ማዘዣ እስከሌለ ድረስ በዩናይትድ ስቴትስ "4ኛው የህገመንግስት ማሻሻያ" ባለኝ መብት መሰረት ወደ ቤቴ እንድትገባ(ቢ) አልፈቅድም።

4ኛው የህገመንግስት ማሻሻያ በሚፈቅድልኝ መብት መሰረት ማንኛውንም ዕቃዎቼን እንድትፈትሽ (ሺ) አልፈቅድም።

ሕገ መንግሥታዊ መብቶቼን መጠቀም ፈልጋለሁ።

እነዚህ ካርዶች ለዜጎች እና ዜግነት ለሌላቸው ሰዎች ይኖራሉ።

# የማህበረሰብ አጋሮች

## የሚከተሉት የማህበረሰብ ድርጅቶች ለቤተሰብ ድጋፍ ይሰጣሉ፡-

Gilchrist Immigrant Resource Center - ጊልክራይስት ማእከል ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ስደተኞች የሚፈልጉትን ነገር የሚያገኙበት ሥፍራ ነው። ማዕከሉ በመንግስት ኤጀንሲዎች እና በማህበረሰብ ድርጅቶች ለሚሰጡ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች መረጃ እና ሪፈራል ይሰጣል። በዚህ ስልክ ቁጥር ይደውሉላቸው፡- 240-777-4940 (www.montgomerycountymd.gov/gilchrist/immigrant-rights/)

"CASA in Silver Spring - CASA de Maryland" ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን በሜሪላንድ ውስጥ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ስደተኞች የህግ አገልግሎት ድጋፍ የሚሰጥ ድርጅት ነው። ዋናው የትኩረት መስክ በኢሚግሬሽን ህግ ዙሪያ ነው። በተለያዩ የኢሚግሬሽን ጉዳዮች፥ የዜግነት ጥያቄ ማመልከቻዎች፣ የቤተሰብ የኢሚግሬሽን አቤቱታዎች፣ የጥገኝነት እና የስደተኛነት ማመልከቻዎች፣ እና ከአገር መባረርን መከላከል የመሳሰሉ የህግ ድጋፎችን ይሰጣሉ። በዚህ የስልክ ቁጥር ይደውሉላቸው፡- 240.491.5763 (www.wearecasa.org/maryland/)

በሲልቨር ስፕሪንግ የሉተራን ማህበራዊ አገልግሎት - ናሽናል ካፒታል አካባቢ የሉተራን ማህበራዊ አገልግሎት (LSSNCA) ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን በሜሪላንድ እና በአካባቢው ሰፊ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫዎች፥ የቤተሰብ ድጋፍ ፕሮግራሞችን እና የኢሚግሬሽን አገልግሎቶችን ለምሳሌ፡- ስደተኞችን መልሶ የማቋቋም እና የኢሚግሬሽን የህግ አገልግሎቶችን ያካትታሉ። በዚህ ስልክ ይደውሉላቸው፡- (202) 723-3000 (www.lssnca.org)

ቤት አልባነትን የማስቆም እና የመከላከል አገልግሎት (SEPH) ፕሮግራም "Housing First philosophy" ቤት አልባነትን መገደብ፣ መቀነስ፣ እና በተደጋጋሚ እንዳይከሰት ለማድረግ የሚሠራ ፕሮግራም ነው። SEPH የመኖሪያ ቤት ችግርን ማቃለል፣ ቤት አልባነትን መቅረፍ፣ እና ቋሚ የመኖሪያ ቤትን ጨምሮ ተከታታይ አገልግሎቶችን ይሰጣል። (www.montgomerycountymd.gov/homelessness/)

ቦልቲሞር የሚገኘው፥"Maryland Office for Refugees and Asylees (MORA) in Baltimore, MD- MORA" በፌዴራል ደረጃ እውቅና ያላቸውን የስደተኞች ማህበረሰብ አገልግሎቶችን ያስተባብራል እና ያስተዳድራል፣ የስራ አገልግሎቶችን፣ የጤና ህክምና ዕርዳታዎችን፣ የወጣቶች ፕሮግራሞችን፣ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስልጠናዎችን ይሰጣል። (www.dhs.maryland.gov/maryland-office-for-refugees-and-asylees/)

ዓለም አቀፍ የነፍስ አድን ኮሚቴ (IRC) በሲልቨር ስፕሪንግ-IRC ለስደተኞች፣ ለጥገኝነት ጠያቂዎች፣ ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች፣ከሥቃይ የተረፉ እና ሌሎች ስደተኞችን በመልሶ ማቋቋም ፕሮግራም ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲገናኙ እና እንዲዋሃዱ ድጋፍ ይሰጣል (www.rescue.org/united-states/silver-spring-md)

Ayuda in Silver Spring - አዩዳ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ስደተኞች ፍትህ እንዲያገኙ እና ህይወታቸውን ለመለወጥ የህግ፣ የማህበራዊ፣ እና የቋንቋ አገልግሎቶችን ይሰጣል።
(www.ayuda.com/legal-services-4/)

"Immigrant & Refugee Outreach Center (IROC)" በጌትስበርግ፣ ሜሪላንድ MD-IROC - "Moving Up Fund" በመሳሰሉ ፕሮግራሞች አማካኝነት የማሰልጠን እና የማማከር እገዛን ጨምሮ ለስደተኛ ቤተሰቦች የመገልገያ ቁሳቁሶችን ድጋፍ ይሰጣል። (www.irocenter.org/programs-for-immigrant-and-refugee-support-dmv)

